3 ፤ አኹንም ፡ እንደ ፡ ጌታዬና ፡ የአምላካችንን ፡ ትእዛዝ ፡ እንደሚፈሩት ፡ ምክር ፥ ሴቶችን ፡ ዅሉ ፡ ከነርሱም ፡
የተወለዱትን ፡ እንሰድ ፡ ዘንድ ፡ ከአምላካችን ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እናድርግ ፤ እንደ ፡ ሕጉም ፡ ይደረግ ።

4 ፤ ይህም ፡ ነገር ፡ ለአንተ ፡ ይገባልና ፥ እኛም ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነንና ፡ ተነሣ ፥ አይዞኽ ፥ አድርገው ።

5 ፤ ዕዝራም ፡ ተነሣ ፤ አለቃዎቹንና ፡ ካህናቱን ፡ ሌዋውያኑንም ፡ እስራኤልንም ፡ ዅሉ ፡ እንደዚህ ፡ ቃል ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡
አማለ ፤ እነርሱም ፡ ማሉ ።

6 ፤ ዕዝራም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ፊት ፡ ተነሥቶ ፡ ወደኤልያሴብ ፡ ልጅ ፡ ወደዮሐናን ፡ ጓዳ ፡
ገባ ፤ ስለምርኮኛዎቹም ፡ ኀጢአት ፡ ያለቅስ ፡ ነበርና ፥ ገብቶ ፡ እንጀራ ፡ አልበላም ፥ ውሃም ፡ አልጠጣም ።

7 ፤ 8 ፤ ምርኮኛዎቹም ፡ ዅሉ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንዲሰበሰቡ ፥ እንደ ፡ አለቃዎቹና ፡ እንደ ፡ ሽማግሌዎችም ፡ ምክር ፡
በሦስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ያልመጣ ፡ ዅሉ ፡ ንብረቱ ፡ ዅሉ ፡ እንዲወረስ ፥ ርሱም ፡ ከምርኮው ፡ ጉባኤ ፡ እንዲለይ ፡
በይሁዳና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ ዐዋጅ ፡ ነገሩ ።

9 ፤ ሦስት ፡ ቀንም ፡ ሳያልፍ ፡ በዘጠነኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በኻያኛው ፡ ቀን ፡ የይሁዳና ፡ የብንያም ፡ ሰዎች ፡ ዅሉ ፡
ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተሰበሰቡ ። ሕዝቡም ፡ ዅሉ ፡ ስለዚህ ፡ ነገርና ፡ ስለ ፡ ታላቁ ፡ ዝናብ ፡ እየተንቀጠቀጡ ፡
በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ፊት ፡ ባለው ፡ አደባባይ ፡ ተቀመጡ ።

10 ፤ ካህኑም ፡ ዕዝራ ፡ ተነሥቶ ፦ ተላልፋችኋል ፤ የእስራኤልን ፡ በደል ፡ ታበዙ ፡ ዘንድ ፡ እንግዳዎችን ፡ ሴቶች ፡
አግብታችኋል ።

11 ፤ አኹንም ፡ ለአባቶቻችኹ ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተናዘዙ ፥ ደስ ፡ የሚያሠኘውንም ፡ አድርጉ ፤ ከምድርም ፡
አሕዛብና ፡ ከእንግዳዎች ፡ ሴቶች ፡ ተለዩ ፡ አላቸው ።

12 ፤ ጉባኤውም ፡ ዅሉ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ መልሰው ፡ እንዲህ ፡ አሉ ፦ እንደ ፡ ተናገርኸን ፡ እናደርግ ፡ ዘንድ ፡
ይገባናል ።

13 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የሕዝቡ ፡ ቍጥር ፡ ብዙ ፡ ነው ፥ ጊዜውም ፡ የትልቅ ፡ ዝናብ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፥ በሜዳም ፡ ልንቆም ፡
አንችልም ፤ በዚህም ፡ ነገር ፡ እጅግ ፡ በድለናልና ፥ ይህ ፡ ሥራ ፡ የአንድ ፡ ወይም ፡ የኹለት ፡ ቀን ፡ ሥራ ፡ አይደለም ።

14 ፤ አለቃዎቻችንም ፡ በጉባኤው ፡ ዅሉ ፡ ፋንታ ፡ ይቁሙ ፤ ስለዚህም ፡ ነገር ፡ የአምላካችን ፡ ጽኑ ፡ ቍጣ ፡ ከእኛ ፡
ይመለስ ፡ ዘንድ ፡ እንግዳዎቹን ፡ ሴቶች ፡ ያገቡት ፡ በከተማዎቻችን ፡ ያሉት ፡ ዅሉ ፡ በተቀጠረው ፡ ጊዜ ፡
ይምጡ ፥ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ የከተማ ፡ ዅሉ ፡ ሽማግሌዎችና ፡ ፈራጆች ፡ ይምጡ ።

15 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የዐሳሄል ፡ ልጅ ፡ ዮናታንና ፡ የቴቁዋ ፡ ልጅ ፡ የሕዝያ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ተቃወሙ ፤ ሜሱላምና ፡
ሌዋዊውም ፡ ሳባታይ ፡ ረዷቸው ።

16 ፤ ምርኮኛዎቹም ፡ እንዲህ ፡ አደረጉ ፤ ካህኑ ፡ ዕዝራም ፡ የአባቶችም ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ በያባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡
ተለዩ ፥ ዅሉም ፡ በየስማቸው ፡ ተጻፉ ፤ በዐሥረኛውም ፡ ወር ፡ በመዠመሪያው ፡ ቀን ፡ ነገሩን ፡ ይመረምሩ ፡ ዘንድ ፡
ተቀመጡ ።

17 ፤ እስከመዠመሪያው ፡ ወር ፡ እስከመዠመሪያው ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ሠረተው ፡ እንግዳዎቹን ፡ ሴቶች ፡ ያገቡትን ፡
ሰዎች ፡ ዅሉ ፡ መርምረው ፡ ጨረሱ ።

18 ፤ ከካህናቱም ፡ ወገን ፡ ልጆች ፡ እንግዳዎቹን ፡ ሴቶች ፡ ያገቡ ፡ ሰዎች ፡ ተገኙ ፤ ከኢዮሴዴቅ ፡ ልጅ ፡ ከኢያሱ ፡
ልጆችና ፡ ከወንድሞቹ ፥ መዕሴያ ፥ አልዓዛር ፥ ያሪብ ፥ ጎዶልያስ ።

19 ፤ ሚስቶቻቸውን ፡ ይፈቱ ፡ ዘንድ ፡ እጃቸውን ፡ ሰጡ ፤ ስለ ፡ በደላቸውም ፡ ከመንጋው ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፡
ለበደል ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረቡ ።

20 ፤ ከኢሜር ፡ ልጆችም ፤ ዐናኒና ፡ ዝባድያ ።

21 ፤ ከካሪም ፡ ልጆችም ፡ መዕሴያ ፥ ኤልያስ ፥ ሽማያ ፥ ይሒኤል ፥ ዖዝያ ።

22 ፤ ከፋስኩር ፡ ልጆችም ፤ ኤልዮዔናይ ፥ መዕሴያ ፥ ይስማኤል ፥ ናትናኤል ፥ ዮዛባት ፥ ኤልዓሣ ።


www.ethiopianorthodox.org

23 ፤ ከሌዋውያንም ፤ የዛባት ፥ ሰሜኢ ፥ ቆሊጣስ ፡ የሚባል ፡ ቆልያ ፥ ፈታያ ፥ ይሁዳ ፥ አልዓዛር ።

24 ፤ ከመዘምራንም ፤ ኤልያሴብ ፤ ከበረኛዎችም ፤ ሰሎም ፥ ጤሌም ፥ ኡሪ ።

25 ፤ ከእስራኤልም ፡ ከፋሮስ ፡ ልጆች ፤ ራምያ ፥ ይዝያ ፥ መልክያ ፥ ሚያሚን ፥ አልዓዛር ፥ መልክያ ፥ በናያስ ።

26 ፤ ከዔላም ፡ ልጆችም ፤ ሙታንያ[235] ፥ ዘካርያስ ፥ ይሒኤል[236] ፥ ዐብዲ ፥ ይሬሞት ፥ ኤልያ ።

27 ፤ ከዛቱዕ ፡ ልጆችም ፤ ዔሊዮዔናይ ፥ ኢልያሴብ ፥ ሙታንያ ፥ ይሬሞት ፥ ዛባድ ፥ ዓዚዛ ።

28 ፤ ከቤባይ ፡ ልጆችም ፤ ይሆሐናን ፥ ሐናንያ ፥ ዘባይ ፥ ዐጥላይ ።

29 ፤ ከባኒ ፡ ልጆችም ፤ ሜሱላም ፥ መሉክ ፥ ዓዳያ ፥ ያሱብ ፥ ሸዓል ፥ ራሞት ።

30 ፤ ከፈሐት ፡ ሞዐብ ፡ ልጆችም ፤ ዓድና ፥ ክላል ፥ በናያስ ፥ መዕሴያ ፥ ሙታንያ ፥ ባስልኤል ፥ ቢንዊ ፥ ምናሴ ።

31 ፤ ከካሪም ፡ ልጆችም ፤ አልዓዛር ፥ ይሺያ ፥ መልክያ ፥ ሸማያ ፥ ስምዖን ፥

32 ፤ ብንያም ፥ መሉክ ፥ ሰማራያ ።

33 ፤ ከሐሱም ፡ ልጆችም ፤ መትናይ ፥ መተታ ፥ ዛባድ ፥ ኤሊፋላት ፥ ይሬማይ ፥ ምናሴ ፥ ሰሜኢ ።

34 ፤ ከባኒ ፡ ልጆችም ፤ መዕዳይ[237] ፥ ዓምራም[238] ፥ ኡኤል ፥

35 ፤ በናያስ ፥ ቤድያ ፥ ኬልቀያ ፡

36 ፤ ወንያ ፥ ሜሪሞት ፥ ኤልያሴብ ፥

37 ፤ መታንያ ፥ መትናይ ፥ የዕሱ ፥

38 ፤ ባኒ ፥ ቢንዊ ፥ ሰሜኢ ፥

39 ፤ ሰሌምያ ፥ ናታን ፥ ዓዳያ ፥

40 ፤ መክነድባይ ፥ ሴሴይ ፥ ሸራይ ፥

41 ፤ ዔዝርኤል ፥ ሰሌምያ ፥ ሰማራያ ፥

42 ፤ ሰሎም ፥ አማርያ ፥ ዮሴፍ ።

43 ፤ ከናባው ፡ ልጆችም ፤ ይዔኤል ፥ መቲትያ ፥ ዛባድ ፥ ዘቢና ፥ ያዳይ ፥ ኢዮኤል ፥ በናያስ ።

44 ፤ እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ እንግዳዎቹን ፡ ሚስቶች ፡ አግብተው ፡ ነበር ፤ ከነዚህም ፡ ሚስቶች ፡ ዐያሌዎቹ ፡ ልጆችን ፡ ወልደው ፡ ነበር ፨

---

235 ዕብ. ፥ መታንያሁ ፡ (መባአ ፡ አምላክ ፥ ያምላክ ፡ ስጦታ ፣ መጥን) ።

236 ዕብ. ፥ ይሒኤል ፡ (የሐዩ ፡ እግዚእ ፥ ጌታ ፡ ይኖራል) ።

237 ዕብ. ፥ መዐዳይ ፡ (ምዕዳው • መሻገሪያ) ።

238 ዕብ. ፥ ዐምራም ፡ (ዐመ ፡ ራማ • የልዕልና ፣ የከፍታ ፡ ሕዝብ)



www.ethiopianorthodox.org